23ኛ ዓመት ቁጥር 21
23nd Year No. 21

ባሕር ዳር ጥቅምት 18 ቀን 2011 ዓ.ም
Bahir Dar, October 28, 2018

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ

# ZIKRE HIG

## Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ 45 ብር
Unit Price Birr 45

## ማውጫ

**አዋጅ ቁጥር 258/2010 ዓ.ም**
**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የየእርከኑን ም/ቤት ተወካዮች ብዛት ለመወሰን የወጣን አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ**

## Content

**Proclamation No. 258/2018**
**A Revised Proclamation for Determining the Number of Council Representatives at Every Level in the Amhara National Regional State**

## አዋጅ ቁጥር 258/2010 ዓ.ም

## በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የየእርከኑን ም/ቤት ተወካዮች ብዛት ለመወሰን የወጣ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

ምርጫ የህዝቡ የስልጣን ባለቤትነት መገለጫ እንደ መሆኑ መጠን ምልዓተ-ህዝቡ የመምረጥ መብቱን በሰፊ ተሳትፎ እንዲያረጋግጥ ለዚሁ የሚረዳውን ምቹ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

## Proclamation No. 258/2018

## A Revised Proclamation Issued to Determine for the Number of Council Representatives at Every Level in the Amhara National Regional State

WHERE AS, it is necessary to create conducive condition that people shall ensure their electorial right through high participation since election is the expression of their supreme power;

በተከታዩ በጀት ዓመት ይካሄዳል ተብሎ የሚጠበቀው የአካባቢ ምርጫ ሂደት የተጀመረውን የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ በሚያጎለብት አግባብ ይከናወን ዘንድ ተገቢውን የቅድመ ዝግጅት ተግባር ማድረግ በማስፈለጉ፤

በክልሉ ውስጥ በስራ ላይ በሚገኘውና የየእርከኑን ምክር ቤት ተወካዮች ብዛት ለመወሰን በወጣ አዋጅ ቁጥር 140/1999 ዓ.ም አንዳንድ ድንጋጌዎች ስር እንደተመላከተው የተመራጮች ቁጥር መብዛቱ ለአስተዳደርም ይሁን ለአተገባበር አደጋች በመሆኑ የተነሳ ለውይይት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የተወሰነ ማሻሻያ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የአማራ ክልል ም/ቤት በተሻሻለው የብሄራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንኡስ አንቀጽ 3 (1) ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን አዋጅ አውጥቷል'

1. **አጭር ርእስ**

ይህ አዋጅ "**የየእርከኑ ምክር ቤት ተወካዮች ብዛት መወሰኛ አዋጅን ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 256/2010** ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ማሻሻያ**

የየእርከኑ ምክር ቤት ተወካዮች ብዛት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 140/1999 ዓ.ም እንደሚከተለው በዚህ አዋጅ ተሻሽሏል።

ሀ) የአዋጁን አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (3) ተከትሎ ከዚህ በታች የተመለከተው አዲስ ንኡስ አንቀጽ (4) የገባ ሲሆን በዚህ ተጨማሪ ድንጋጌ መግባት ምክንያት ንኡስ አንቀጽ (4) የነበረው ንኡስ አንቀጽ (5) ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡

WHERE AS, it is needed to make the necessary preparation for the local election process, which is expected to be carried out by the next fisical year, could be implemented in a way that can enhance the democratic building system;

WHERE AS, it is found necessary to make some amendments on the existing proclamation No.140/2006 issued to provide the number of council representatives at every level has limitations for its implementation due to its greater number as it is indicated in some provisions;

NOW, THEREFORE, the council of the Amhara National Region in accordance with the power vested in it under the provision of Article 49 sub-article 3(1) of the Revised National Regional Constitution issued this proclamation.

## 1. Short Title

This proclamation may be cited as "**Amendment Number Determination of Council Members at Every Level Proclamation No. 256/2018**."

## 2. Amendment

Proclamation Number 140/2006 Council Representatives Number of Every Level Determination is amended herewith as follows:

A. Where as new sub-article (4) is added following article 2, sub-article (3) of the proclamation; due to this, and the previous sub-article (4) is forwarded as being sub-article (5).

4. የመሪና ንኡስ ማዘጋጃ ቤት ደረጃ ያላቸው ከተሞች ምክር ቤቱ የህዝቡን ብዛት መሰረት በማድረግ ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ባላቸው ከተሞች አንድ ወኪል በአማካኝ ከ1000 እስከ 1500 ህዝብ እንዲሁም ዝቅተኛ የህዝብ ቁጥር ባላቸው ከተሞች አንድ ወኪል በአማካኝ ከ200 እስከ 250 ህዝብ እንዲወክል ሁኖ ከ60-120 ተወካዮች፡

ለ) በአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (4) በዚህ አዋጅ ንዑስ አንቀጽ (5) ሆኖ የተሸጋሸገው፤ እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

5. ለቀበሌ ም/ቤት የህዝቡን ብዛት መሰረት በማድረግ ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ባላቸው ቀበሌዎች አንድ ወኪል በአማካኝ ከ60 እስከ 70 ህዝብ እንዲሁም ዝቅተኛ የህዝብ ቁጥር ባላቸው ቀበሌዎች አንድ ወኪል በአማካኝ ከ2 እስከ 5 ሰዎች እንዲወክል ሆኖ ከ100-200 ተወካዮች፤

## 3. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

*ባህር ዳር*

*ጥቅምት 18 ቀን 2010 ዓ.ም*

*ገዱ አንዳርጋቸው*

*የአማራ ብሔራዊ ክልል ፕሬዝዳንት*

4. For towns having a level of leading and sub-municipality, the council based on the number of the population, in populous towns one representative for 1000 to 1500 people on average as well as in scarely populated towns one representative for 200 to 250 people on average, the total being from 60 to 120 representatives.

B. In the proclamation, Article 2 sub-article (4) which is forwarded as being sub-article (5) in this proclamation is amended as follows:

5. For kebele council, on the basis of the number of the population, in populous kebeles one representative for 60 to 70 people on average as well as in scarely populated kebeles one representative for 2 to 5 people on average, the total being from 100 to 200 representatives.

## 3. Effective Date of the Proclamation

This proclamation shall come into force since its publication date in the Regional State Zikre-Hig Gazette.

**Done at Bahir Dar**

**This ----- Day of October 2018**

**Gedu Andargachew**

**President of the the Amhara National Region.**